የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ መስከረም ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st Year No. 7
ADDIS ABABA October 7, 2008

ማውጫ

የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች ማስተላለፍ አዋጅ.........................................ገጽ ፩

CONTENT

City Government Grievance Organs Transfer of the City Government Houses Proclamation ........... Page 1

## አዋጅ ቁጥር ፯/፪ሺ፩

## የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ

የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነትና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ (እንደተሻሻለ) በልዩ ሁኔታ ታይተው ቤት ማግኘት የሚገባቸው ተጠቃሚዎችን ጥያቄ ከዕጣ ውጭ ማስተናገድ የሚያስችል አሰራርን ባካተተ መልኩ እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬/፩/ሀ መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ ‹‹የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ እንደገና (እንደተሻሻለ) ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፯/፪ሺ፩ ዓ.ም.›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## Proclamation No. 7/2008

## A Proclamation to provide for the Responsibilities of the City Government Houses and its Execution Proclamation No. 19/2005 Re-amendment Proclamation

**WHEREAS,** it has become necessary to re-amend the proclamation to provide for the Responsibilities of the City Government Organs in the Transfer of the City Government House and its Execution Proclamation No/ 19/2005 (as amended) in order to develop a system in which home seekers exceptionally acquire houses without casting lot;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 14(1) a of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003, the City Council hereby Proclaims as follows;

***1. Short Title***

This Proclamation may be cited as "A Proclamation to Provide for the Responsibilities of the City Government Organs in the Transfer of the City Government Houses and its Execution Proclamation No. 19/2005 re-amendment Proclamation No. 7/2008".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.90

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

፪. <u>ማሻሻያ</u>

የከተማው አስተዳደር አካላት የአስተዳደሩን ቤቶች የማስተላለፍ ኃላፊነታቸውንና አፈፃፀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፺፯ (እንደተሻሻለው) እንደሚከተለው በድጋሚ ተሻሽሏል።

በአዋጁ አንቀጽ ፮ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፭/ ተጨምሯል።

፭. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ /፩/ እስከ /፬/ የተደነገገው ቢኖርም፣ የከተማው ካቢኔ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የቤት ፈላጊዎች ከዕጣ ውጭ በልዩ ሁኔታ ሊስተናገዱ የሚችሉበትን ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከመስከረም ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ**
**መስከረም ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.**

**ኩማ ደመቅሳ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

2. *Amendment*

The Proclamation to provide for the Responsibilities of the City Government Organs in the Transfer of the City Government Houses and its Execution Proclamation No. 19/2005 (as amended) is further amended as follows:-

The following new sub-article (5) is added under Article 6 of the Proclamation.

5. Notwithstanding the provisions of sub-Article (1)-(4) of this Article the City Cabinet where it finds necessary may issue regulation to provide for home seekers exceptionally acquire houses without casting lot.

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 7th day of October, 2008.

**Done at Addis Ababa**
**This 7th day of October, 2008**

**Kuma Demeksa**
**Mayor of Addis Ababa City**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ